<u>እየተስተዋለ --ጻግም ማሳሰቢያ</u>

ምከረው ምከረው እምቢ ሲል መከራ ይምከረው ከመባሉ በፊት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ዜጎች አደብ ገዝተው፤ ግለኝነትን ሸብበውና ሀገርን አስቀድመው እንዲገኙ እንደገና ማሳሰብ የግድ ሆኗል። ይህ ማሳሰቢያ የሚመለከታቸው በባዕድ ሀገር ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገር እየተመለሱ አውቀወም ሆነው ሳያውቁ የወያኔ አገዛዝ ተባባሪ የሚሆኑትን ነው። ተባባሪ ስንል ወደ ሀገር ተመልሰው የሕዝብ ንብረትና መሬትን እየገዙ የወያኔ አገዛዝን ኪስ የሚሞሉትን ነው።

የወያኔ አገዛዝ ዜጎችን ከቤታቸው እያፈናቀለ ቤቶቹን እየሸጠ እንዳለ የአደባባይ ምስጢር ነው። ባለቤት የላቸውም ተብለው በየአካባቢው የሚሸጡት የእርሻ ቦታዎችም ባለቤቶቻቸው የተባረሩባቸው መሆናቸውም ይታወቃል። አርሶ አደሮችንም ማፈናቀል ከሰንዳፋ እስከ አዋሳ ወዘተ እየተካሄደ ያለ ህገ ወጥ ድርጊት መሆኑንም ዜጎች በምሬት ያጋለጡት ጉዳይ ነው። ጊዜ ተለወጠኩ አለና በዘመነ ደርግ ያልነበረው የስደተኛ ወደ ሀገር ተመልሶ ጉዞ በዛ--በርከት ማለቱን መታዘብ ተገደናል። አንዳንዶች ይባስ ብለው ወያኔ በስልጣን እያለ አካባቢያችንን እናለማለን ብለው ደፋ ቀና ማለቱን ከተያያዙት ጊዜ አልፏል። ሰንኮፋው ሳይነቀል ያሽረናል ብሎ መቃዠቱ ዛሬም ያለ ነው። ዜጎች ወዳጅ ዘመድ ለማየት መጓጓታቸው እንዳለ ሆኖ ይህ ሀገር የመመለሱ ዕድል ለሁሉም ዜጋ ክፍት ያልሆነና በፖለቲካው መስክ ፀረ ወያኔ ለሆኑት ብዙዎችም የተነፈገ መሆኑ ደግሞ የሚዘነጋ አይደለም። ያም ሆነ ይህ ፍዳ እየቀመሰ ባለው ሕዝባችን ላይ እንደ ባዕድ ጎብኚ ሊሆኑበት የሚከጅላቸውን ዜጋዎች መውቀሰ ሲያንስ ነው። በስራም ሆነ በብድር የተገኘን ገንዘብ ይዞ ድህነት ባጠቃው ሕዘባችን ላይ እንደ ባዕድ መዘባነኑ ሆነ በወጣት ሴቶች ላይ መባለጉ ከኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ አለመሆኑ መነገር ያለበት ሆኗል። ያሳዝናል፤ያጠያይቃልም።

ከሁሉም በላይ ከፍቶ ያለው ግን ከወያኔ አገዛዝ ጋር በኤኮኖሚው መስክ የሚደረገው ትብብር ነው። ይህ ትብብር ውሎ አድሮ ሳይሆን ከመ ቅፅበትም ፖለቲካዊ አንደምታ ያለው ነውና በዚህ ትብብር የሚሰማሩት አገዛዙንም ወደዱ ጠሉ የመደገፍ ወይም የመጨመትና የጨዋ--ስልጡን ፖለቲካ ማለትም የመጎንበሰ ፖለቲካ አቀን

ቃኝ ይሆናሉ፡፡ በከተሞች ወያኔ የሚሸጠው ቤትና ቦታ የራሱ አይደለም፡፡ እንኳን በአዲስ አበባና ሌሎች ከተሞች ቀርቶ በመቀሌና አድዋም ቢሆን የመለስ መንጋ የሚሸጠው የራሱ መሬትና ቤት የለውም፡፡ ዜጎች በዚህም በዚያም ቤታቸውን እየተ ቀሙ፤ከንብረታቸው እየተፈናቀሉ ቤታቸው ለሽያጭ ሲቀርብ ከባዕድ የተመለሱ በዶላርና ኤሮ ገንዘብ ጉልበት ተማምነው የሰዉን ቤትና ቦታ እየገዙ ናቸው፡፡ ይህ ባለቤትነታቸው ሊፀና የሚችል አለመሆኑን መገንዘብ እንዴት እንደቃታቸው ቢገር ምም ባለቤትነታቸው ከመለስ አገዛዝ ጋር አብሮ የሚያከትም መሆኑ ግን አከራካሪ አይደለም፡፡ በሰው ቤት ባለቤት ነን ብለው የሚኖሩ በየወያኔ ካድሬዎችና ደጋፊዎ ችና ቅጥረኞችም ቢሆኑ ማንነታቸው ከሕዝብ የተሰወረ አይደለምና ነግ ቀውጢ ቀን ስትመጣ ከቤታቸው በጤና መውጣታቸው አጠራጣሪ ነውና ከዛሬው ሊያሳስባ ቸው ይገባል፡፡ እየተስተዋለ ብለን ማሳሰቢያ ስናሰማ ከዛሬው አስረሽ ምቺውና የዕ ብሪት አገዛዝ ድንፋታ ባሻገር ነገ ይዛ ልትመጣ ያረገዘችውን በማየት ነውና ማዳመ ጡና ተገቢውን እርምጃ መውሰዱ አስፈላጊ ነው፡፡ የቀድሞው አምባገነን ቅጥረኞቹ ን ይዞ ዚምባብዌ አልተሰደደም፡፡ ቃሊቲ ያሉ ጓደኞቹ የተረፉት ሊያረጋግጡት የሚችሉት ሀቅ ነው፡፡ መለስ ዜናዊና የቅርብ ጓደኞቹም የተለየ አያደርጉም፡፡ ሕዝብ ሀገሩንም ንብረቱንም ያስከብራልና ህገወጥ ሁኔታዎች ሁሉ ከህገወጥ አገዛዝ ጋር አብረው የሚወገዱ ይሆናሉ፡፡ ሚሊዮን የሕዝብ አፎች ቢሸበቡም ሚሊዮን የሕዝብ ዓይኖች አልተዘጉም፡፡ እየተሰተዋለ ማለት ወቅታዊ ነው፡፡